# የቅጥረኛን ምላስ ማን ያናግረዋል? የቀጣሪው ገንዘብ!

## ወቅታዊ ሀተታ ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ

ደግመን ደጋግመን ማሳሰቢያም ማስጠንቀቅያም በሚል ወያኔ ድርጅቶችን ለማፍረስ ሆነ ሕዝብን ለመከፋፈል የሚጠቀመው በሀይል ብቻ ሳይሆን በሰርጎ ገቦችና ቅጥረኞች አማካይነትም ነው ብለን ነበር። ይህ ነጥብ የሚያስፈልገውን ትኩረት ያገኘ አይመስልም። ምክንያቱም ወያኔ ዛሬም ቅጥረኞቹን አሰማርቶ እየጎዳን ነውና ነው።

ወያኔ ትግል የሚለውን ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ለምሳሌ ኢሕአፓን ሰርጎ ገብቶ ለመጉዳት አያሌ ጥረቶችን አድርጎ ነበር። ዋና ዋና እና በርካታዎቹን ድርጅቱ ነቅቶባቸው ከነአሰማሪዎቹ አክሽፏቸዋል። በ ኢሕዴኅና ኢዲኅም ውስጥ ሰርጎ ገቦቹን ሰዶ ብዙ ጉዳት አድርሷል። ጠላት ባለው ደርግ ላይም እንዲሁ በተለይም በጠባብ ብሔረተኛነት የለክፋቸውን ቅጥረኛው በማድረግ። ወያኔ በዚህ መስክ ረቂቅም ባለከፍተኛ ስልትና ባለችሎታም አይደለም፤ አልነበረምም። በገንዘብ ይገዛል፤ በዘር ደልሎ ያሰማራል፤ ስልጣን ጥመኞችንም በሹመት ያቋምጣችውና ወጥመድ ከቶ ጓዶቻቸውንም አሳልፈው እንዲሰጡ ያደርጋቸውና ተጠቅሞባቸው ይወረውራቸዋል። በኢሕአፓ የሰሜን አሜሪካ መዋቅር ሀላፊነት የነበረው ግለሰብ፤ ታጋይ ጓደኞቹን ኣሳልፎ ሰጥቶ ተራ ሚኒስቴርነትን ቦታ ያገኘው አፋሩ መሃሙዳ ጋስ፤ ከኦነግ በላይ የኦሮሞ ጽንፈኛ ነኝ ያለው ጋዜጠኛ ዛሬ የሻዕቢያ ውዳቂ ሰላይ መሆኑ የተጋለጠው ማፈሪያ ግለሰብ፤ ጸረ ወያኔ ነኝ ብሎ ውሎ አድሮ የተመጻደቀው ነፍሰ ገዳይ ወያኔና ያው ውሎ አድሮ ማንነቱን ማለትም መጥፎ ወያኔነት የተጋለጠው ብስራት አማረ፤ ወያኔ ጃስ ሲለው ሊናከስ የሚነሳውና በታጋይ ድርጅቶች ላይ ጸረ ወያኔና ምስጢር አዋቂ መስሎ የሚቀባጥረው የታወቀ ለፍላፊና ዋሾ ወዘተ ወዘተ--ነቃ ብለን ካጤንን ራሳችን ያስጠቃነው ራሳችን በራችንን ከፍተን ተጫወቱብን ብለን ነው ቢባል ስህተት አይሆንም።

ቅጥረኞችና ሰርጎ ገቦችን ማወቅና ማጋለጥ ከባድ አይደለም። ድርጅቶች የራሳቸው መከላከያ ያስፈልጋቸዋል። መዝረክረኩ መቆም አለበት ማለት ነው። እንዲያውም ታጋይ ድርጅቶች ወያኔን ሰርገው መግባቱ ዋናው ትኩረታቸው ከሆነ ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል ብቻ ሳይሆን ወያኔንም ያጠቃሉ፤ ይጎዳሉ። በሕዝብ ደረጃ ደግሞ በመድረክ አለን አለን የሚሉት ብቻ ሳይሆኑ ድምጽ አጥፍተው የሚሰሩትንም የወያኔ ቅጥረኞች ማወቁ ከባድ አይደለም። በቅድሚያ ስራቸውን ማወቅ ያስፈልጋል። ስምሪታቸው ማንን እየጠቀመ ነው ብሎ መመርመሩ ወሳኝ ጉዳይ

ነው። ምንኛ ጸረ ወያኔ ነኝ ብሎ ሽፋን ቢያዘጋጅም ዋናው ስራ ወሬ ለቀማ፤ ታጋይ ድርጅቶችን ማጥቃት፤ ጎጂ አሉባልታ ማሰራጨት፤ አለአቅሙ ተንደላቆ መኖር ከሆነ ግለሰቡን ማጥናት የግድ ይሆናል። ግራ ቀኙን ወያኔ ለማለት መነሳትና መታመስም ባይገባም ግን ጆሮን ከፈት፤ ዓይንን ከፈት፤ ንቃትን ከፍ ማድረጉ ተገቢ ነው። ቅንጅትን ያፈረሰው ክህደቱ ብዙ ዜጋን አወናብዷል-- የወያኔ ቅጥረኛ ነው ያሉት ሰሚ አጥተው ነበር። ጋዜጠኛ ነኝ ባዩና ገብረ ርኩሱ የሻዕቢያ ሰላይ ኢትዮጵያዊ መስሎ ሲተራመስ ሀሰተኛ ነው አትመኑት ሲባል በርካታ ምሁሮች የሰላዩ ጠበቃ ሆነው አጋላጮቹን ሲያወግዙ እንደነበርም ማስታወስ ይቻላል። ቅጥረኛ እውቁኝ ተገዝቻለሁ ብሎ ሁሌም አይመጣም። መደበቅና ማስመሰል ትጥቁ ነው/ትጥቋ ነው። ለዚህ ስራ የሚመለመሉት ደግሞ የማይመስሉ፤ ክህዲ መቸም አይሆኑም የሚባሉት ናቸው። ጭምብላቸውን ሳይጋለጡም አያወልቁም። የሚሰጣቸው ስልጠና ደግሞ አክራሪ ጸረ ወያኔ መስለው እንዲሰለፉና መድረክም እንዲያጣብቡ ነው። ግን ዋና ተልኮአቸው ታጋይ ድርጅቶቻ መሪዎችን ማጥቃት፤ ክፍፍልን ማራገብ ነውና ትኩረታቸው የት ነው፤ ማንን በቅድሚያና በዋና ደረጃ እያጠቁ ነው ለሚለው መልስ ስናገኝ ስምሪታቸው ለማን መሆኑን ማወቅ እንችላለን። ጸረ ወያኔ ነን ብለው የሚጠበቀውን ቢለፍፉም ዋናው ጥቃታቸው ማንን ይጎዳል ብሎ መመርምሩ የቅጥረናኛ ስራ እየሰሩ ያሉትን ያጋልጣል።

ሁሉም ቅጥረኛ ተቀጣሪ አይደለም። አንዳንዱ ጅል ከመሆኑ የተነሳ፤ በውሱን የግል ጥቅም ታውሮና በጥላቻ ተተራምሶ ዓይነ ህሊናው ይታወራልና  ወያኔ ተጠግቶ ሳይቀጥረው የወያኔን ስራ ሲያሰራው ይገኛል። ይህ ዓይነቱ ደግሞ አደገኛ ነው-- ሞኝ ካመረረ በሬ ከደነበረ ዓይነት ማለት ነው። ኢሕአፓን የሚጠሉ ሽብርተኞችና የተደበቁ ወንጀለኞች ድርጅቱን ያጠቁ መስሏቸው፤በወያኔ እርዳታ ይጠፋል መስሏቸው ወያኔን በሚረዳ መልኩ ድርጅቱን ነጋ ጠባ ያጠቃሉ። ሩቅ ሳይሄዱ ግን ወያኔ በወጥመዱ ያስገባና ተቆጣጥሮ ያሰማራቸዋል፤ ቅጥረኝነታቸውም የጸደቀ ይሆናል። ባይሆንም ያው ባደቆናቸው ሰይጣን ቄስ እስኪባሉ ቀጣይ ናቸው። የታጋዩ ጎራ ለጥቃት የሚዳረገው በወያኔ ብቻ ሳይሆን ወያኔን በሚደግፉ ባዕዳንም ነው። አሜሪካ ወዳጆቿን ሳይቀር ስትሰልል ተገኝታለና፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በአሜሪካ የስለላ ተቋሞች ሰላይና አስተርጓሚ ተብለው ተቀጥረዋልና አሜሪካ በምድሯም ሆነ ቤሎች ቦታዎች ያሉትን ኢትዮጵያውያን እየሰለለች  መረጃ ለወያኔም ታቀብላላች። እስራኤልና እንግሊዝም ይሰልሉናል ፤ ወዘተ... ስለዚህም የነዚህ ሁሉ ቅጥረኞች እየሰረሰሩ ሊያፈርሱን እየጣሩ መሆናቸው መታወቅ አለበት--አለበት ብቻ ሳይሆን የሚጠበቅም ነው። ይህን ሁሉ ለመቋቋም ንቃት አስፈላጊ ሲሆን በርን መዝጋትና ምስጢርን መጠበቅ ደግሞ ዋና ነው። አላፊ

አግዳሚውንና አፈኛውን ወደ ታጋይ ጎራ ዘው አድርገን ካስገባንና በተለይም ቀፈፈን የሚሉትን በመቃወም ለቅጥረኛ ጥብቅና ከቆምን ጉዳታችን ከፍ ይላል። ጃተኔ ወይም መባ ጽዮን በናይሮቢ በወያኔ የተገደለው ቅጥረናውን ቡዮ አምኖና ወዳጅ ብሎ በማስጠጋቱ ነው። ፕሮፌሰር አሥራት፤ አሰፋ ማሩና ሌሎችም በቅጥረኞች ተጎድተዋል። እነ ጸጋዬ ደብተራው በወያኔ የተጠቁት በከሀዲ ተጋልጠውና ተጠቅተው ነው። ቀደምም አንጃ ሆኖ ስንት ጉዳት ያደረሰው ብርሀነ መስቀል ለፖሊስ መርማሪዎች በሰጠው ሰፊ ገለጻ ከሟቹ ጌታቸው ማሩ ጋር ተባብሮ ምንኛ ድርጅቱን ሊጎዳና ሊያፈርስ እንደጣረ ግልጽ አድርጓል። ሳይጠሩት አቤት ያለ አንጃ ሆኖ፤ ወዶ ገባ የደርግ ባንዳ ሆኖ ብዙ ሕይወት ማስጠፋቱን ዛሬ በወያኔ የጓዳ ረዳትነት በሚጻፉ መጽሃፍት ሊደበቅ የሚችል አይደለም/አልሆነም።

የቅጥረኛ  ምላስ የሚንጣጣው ለቀጣሪው ነው። ተልዕኮ ነውና አፍ ማዳጡ ድርጊት መጋለጡ አይቀሬ ነው-- ሁኔታውን የሚከታታል ካለ። ሁሌም ዋና ጥያቄ መሆን ያለበት እርግጠኛ አቅዋሙ ምንድነው፤ ድርጊቱስ ለማን ይጠቅማል ብሎ መመርመር ነው። ይህ ከተደረገ አብዛኞቹ ቅጥረኞች ይጋለጣሉ፤ ይታወቅባቸዋል ማለት ነው። የሁሌ ተላላ ከሆንን ግን ጨካኙ ወያኔ ይጫወትብናል፤ ያጠቃናል ይጎዳናል። ምሳሌዎች ሞልተውናል--ስም መጥቀስም ቢባል ተረኛው ብዙ ነው። ስምሪታቸው ጸረ ህዝብ መሆኑን አውቀን ሌላ የማናውቀው ከሚልክብን ይህንኑ ያላወቅን መስለንና የሀሰት መረጃ እየመገብን አውቀን መቀጠልም ይቻላል። ሰርጎ ገብን የመቋቋሙ ዘዴ ብዙ ነው። የማያውቀው ከሚያውቀው መጠየቅና ፣ መማር አለበት። ሁሉም ታጋይ ድርጅት ግንባር ምስረታና ህብረት ቢያቅተውም አንዱ የሌላውን ምስጢርና ደህንነት መጠበቅ አለበት። አንዱ ድርጅት በወያኔና ቅጥረኞቹ ሲጠቃ፤ ርብርቦሽ ሲደረግበት ሌሎች በዝምታ የሚያዩበት ወይም ከአጥቂዎቹ ጋር የሚተባበሩበት--በግልጽም ይሁን በእጅ አዙር--ጥቃቱን የሚደግፉበት ሁኔታ መኖር የለበትም። የወያኔ ጥቃት ሁሉንም በኢላማነት ያስገባ ነውና። አንድ ታጋይ ድርጅት በወያኔ ተጠቅቶ መዳከሙ የሕዝብ ትግልን ይጎዳልና፤ ያንዱ ድርጅት መድከም ለቀሪው ጉዳት እንጂ አጠናካሪ አይደለምና። ይህን ሀቅ መገንዘብና በጋራ ጸረ ወያኔውን ትግል ማጠናከርና ጸረ ድርጅቶችን መቋቋም አስፈላጊ ነው።

ትግላችን ይፋፋም!!